# የሺ ግጥም እድሜ



በድሉ ዋቅጅራ

# የአምስት ግጥም አድማ

## እና ሌሎች አሜጭር ልብወለዶች

በድሉ ዋቅጅራ

## የደራሲው ቀደም ያሉ መጻህፍት

- በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፣ 1996 አ.ም.
- ፍካት ናፋቂዎች (የግጥም ስብስብ) 1999 አ.ም.
- እውነት ማለት የእኔ ልጅ (የግጥም ስብስብ) 2004 አ.ም.
- ያልተከፈለ ስለት (የአጫጭር ልቦለድ ስብስብ) 2006 አ.ም.
- አገሬ ገመናሽ (መጣጥፎችና ወጎች) 2007 አ.ም.
- የተስፋ ክትባት (የግጥም ስብስብ) 2008 አ.ም.
- የማይጻፍ ገድል (ማስታወሻ) 2009 አ.ም.
- የወይራ ስር ጸሎት (የግጥም ስብስብ) 2010 አ. ም.
- ጠርዝ ላይ፣ 2010 አ.ም.
- የራስ ምስል (የግጥም ስብስብ) 2013 አ.ም.
- ችካል እና እርምጃ (ረዥም ልቦለድ) 2013 አ.ም.

ለ
'ሎራ'

© በድሉ ዋቅጅራ 2014 ዓ.ም
የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

© 2022.
All Right Reserved.

የመጀመሪያ እትም ሰኔ 2014 ዓ.ም.

የሽፋን ስእል፣ ዐብይ ተስፋዬ

አዲስ አበባ፣
ኢትዮጵጵያ።

# ምስጋና

ለ

ፎዚያ መሐመድ (ቹቹ)፣

እንዳለጌታ ከበደ፣

እና

ህይወት ተፈራ

# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. ጨረር፣ ጥብቆና እግር | 7 |
| 2. የመግዛት ሰንሰለት | 27 |
| 3. የእድር ቁና | 49 |
| 4. የአምስት ግጥም እድሜ | 67 |
| 5. የሞላ 'ለት | 143 |
| 6. አጎቴ የመጣ 'ለት | 183 |

# ጨሬር፣ ጥብቆና እግር

‹‹ጤና ይስጥልኝ፤ አቶ እንዳለ፡፡››
‹‹ወይዘሮ እመቤት ጤና ይስጥልኝ፡፡››
‹‹አቶ እንዳለ ደህና አደሩ፡፡››
‹‹ደህና አደሩ መምህር፡፡››
‹‹ሀይ ጋሽ እንዳለ፡፡››
‹‹እንደምን አደርክ፤ ልጅ ጉርሙ፡፡››

ከጥበቃ ስራዬ የተረፈኝ ሰላምታ ነው፡፡ የመምህሩንና ሠራተኛውን አልፎ አልፎም የተማሪ ሰላምታ እመልሳለሁ፤ ብዙ ጊዜ በአደረ አፌ፡፡ እዚህ ትምህርት ቤት በጥበቃ ስራተኛነት ከተቀጠርኩ አስራአራት ዓመት ሆኖኛል፡፡ በእነዚህ አመታት አንድ ሽቦ የሚቆርጥ ጎረምሳ አባርሬያለሁ፡፡ እሱ የቆረጠው የሽቦ አጥር ገብተው የትምህርት ቤቱን ሳር የጋጡ ሶስት ላሞችን በአፈላማ ይዣለሁ፡፡ በተቀር የየቀኑ ስራዬ ከጨሬር ሌቦች ተማሪዎችን መጠበቅ ነው፡፡

‹ስምን መልአክ ያወጣዋል› ለእኔ ያላለው አባባል ነው፤ በሃምሳአንድ አመቴ አንድም እንዳልኩት የሆነልኝ ነገር የለም፡፡ ገቢ ወጪው፣ አላፊ አግዳሚው፣ ‹ጋሽ እንዳለ›፣ ‹እንዳለ›፣ ‹አቶ እንዳለ›፣ እያለ በአፍ አመል ሰላምታ ሲወጥረኝ፣ የእኔን ስም ያወጣው ዲያብሎስ ይመስለኛል፡፡

እዚህ ተፈሪ መኮንን ቴክኒክና ሙያ ተቋም ሰላምታ ለብዙዎች የአፍ አመል ነው፡፡ አንዳንዱማ የጥበቃ የቆርቆሮ ጎጆዬን ነው ሰላም የሚለው፤ የአፍ አመል፡፡ ለእኔ ሥራ ነው፤



‹‹አየህ እንድዬ፣ ጥብቆህ ዛሬ በቁምጣና ሹራብ ተቀይሯል፡፡ ነገ እንደ ተድላ ቦላሌ ሱሪ፣ ሸራ ጫማ፣ ኮት ሸሚዝ ትለብሳለህ፡፡ ከዚያ በኋላ ትልቅ ስትሆን ደግሞ እንደባሻ እጅጉ የፖሊስ ልብስ፣ ወይም እንደ አቶ ሽብሩ ሱፍ ኮትና ሱሪ ልትለብስ ትችላለህ፡፡ ዋናው ልብስህ ኪስ አለማጣቱ ነው፡፡ ኪስ ካለው ዛሬ እየዘገንክ ትበላለህ፡፡ ነገ ትልቅ ስትሆን እየገዛህ ትበላለህ፡፡ ልብስና ኪስ አትጣ የኔ ልጅ›› ግንባሬን ሳመችኝ፡፡ ጥብቆ - የልብስና ኪስ - የኑሮ መሰረት መሆኑ፣ ለመኖር ልብስ ብቻ ሳይሆን ኪስም እንደሚያስፈልግ ያን እለት ገባኝ፡፡››

፤፤፤፧፤፧

‹‹ማለት ... የህይወት ግቡ መኖር ነው፡፡ እያንዳንዱን ቀን መኖር፡፡ እያንዳንዱ ቀን ደግሞ ጥያቄ ነው፤ በመኖር የሚመለስ፡፡ እንደመልሳችን ኑሯችን ይለያያል፡፡ የተለያየ እንጂ የተሳሳተ መልስ ብሎ ነገር የለም፡፡ ... ሞት ለእያንዳንዱ ቀን ጥያቄ መልስ አለመፈለግ ነው፡፡ በህይወት ካለሽ መልስ አለሽ፡፡ የየቀኑ ጥያቄያችን ይመስለኛል የህይወታችን ሚዛን፡፡››

ዋጋ 225.00 ብር

እታፍዘር አታሚዎች +25111 471 12 22